# የተቃዋሚ ፖለቲካ ኃይሎች ተቋማዊ ድክመት ወይስ የራዕይና ስትራተጂ ልዩነት?

በጋሻው አለሙ

## 1) ውስጣዊ ድክመት ወይስ ልዩነት?

በቀዳሚው ጹሁፌ "የተቃዋሚ ፖለቲካ ኃይሎች በድረ-መለስ ኢትዮጵያ፣ አይዲዮሎጂካል እና ስትራተጂካዊ ሁኔታዎች" እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ05/01/2013 በጎልጉል የድረገጽ ጋዜጣ ላይ በወጣው ላይ ተመስርተው አቶ አንዱ አለም ተፈራ በፈረንጆቹ አቆጣጠር 10/01/2013 በጎልጉል የድረገጽ ጋዜጣ ላይ "የተቃዋሚ ፖለቲካ ኃይሎች የተግባር ድክመት ወይንስ የግብና የእቅድ ልዩነት" ብለው ባወጡት ጹሁፍ ላይ ገንቢና አስተማሪ ሃሳቦችን ስላቀረቡ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሰዎት እላለው::

የዚህ ጹሁፍ አላማ በዋናነት በመጀመሪያ ጹሁፌ ላይ ያቀረብኩትን ሃሳብ በበለጠ የሚያብራራ ሲሆን፣ በተጨማሪም በአቶ አንዱ አለም ከተነሱት ገንቢ ሃሳቦች መካከል በበለጠ መብራራት አለባቸው ብዬ ያሰብኳቸውን ጉዳዮች ለመዳሰስ ነው::

በተቃዋሚ ኃይሎች የሚታየው መሰረታዊ ችግር ሁለንተናዊ ውስጣዊ ድክመት እንጂ የርዕይ፣ርዕዮተ አለማዊ አሊያም የስትራተጂና የታክቲክ ልዩነት አይደለም:: በተቃዋሚ ኃይሎች የሚታይ መሰረታዊ ርዕዮተ አለማዊ ስትራተጂያዊ ድክመቶችን በቀደመው ጹሁፌ ለማመልከት ሞክሬያለው:: አይደለም በተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች ይቅርና በሁለት ሰዎች መካከል ለተወሰኑ ነገሮች ላይ ባላቸው አቋም ሊለያዩ ይችላሉ:: ልዩነት በመሰረታዊ ደረጃ ተፈጥሮአዊ ነው:: ነገር ግን፣ የሰለጠነ የፖለቲካ ባህል ልዩነቶችን አቻችሎ፣ የጋራ አጀንዳዎችን ነድፎና በሚያስማሙ ጉዳዮች ላይ በጋራ እየመከሩ ሁሉንም ተሳታፊ አካላት ተጠቃሚ የሚያደርግ እርምጃዎችን መውሰድ የሚጠይቅ ነው::

በኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች መካከል የሚታየው ችግር ግን ይህ የሰለጠነ የፖለቲካ ባህል እጦት ነው:: በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ በምርጫ ቦርድ ተመዝግበው የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ ከ70 በላይ ናቸው:: በትጥቅ እንቅስቃሴና በስደት ላይ የሚገኙ ፓርቲዎች ብዛታቸው ወደ 35 የሚጠጉ ናቸው:: ሁሉም ማለት በሚያስችል ደረጃ እርስ በእርሳቸው ከሚያስማማቸው ጉዳዮች ይልቅ የሚያለያያቸው ይበዛል:: እነዚህ ልዩነቶች ምንጫቸው ግን ተቋማዊ አቅምና ውስጣዊ ዴሞክራሲ እጦት ነው እንጂ የግብና የዕቅድ ልዩነቶች አይደሉም::

በአሁኑ ሰአት ኢትዮጵያ ያለችበትን ፓለቲካዊ ሁኔታ የማይገነዘብ አንድም የተቃማዊ ኃይል የለም:: ሁሉም በሚያወጣቸው ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ ድርጅታዊ ማኔፌስቶዎችና ፖለቲካዊ ትንታኔዎች ላይ ይሄን ሁኔታ መገንዘብ ይቻላል:: በቅርቡ ዶ/ር ነጋሶና ዶ/ር እሸቱ ያወጧቸውን ጹሁፎች መመልከት ከበቂ በላይ ነው:: ድህረ ገጽ ያላቸውን ተቃዋሚ ኃይሎች ለሚጎበኝ ሰው የሚገነዘበው አንደ ነገር ቢኖር ሁሉም ***"የፖለቲካ ስርአት"*** ለውጥ ለማምጣት የሚተጉ መሆናቸውን ነው:: በጹሁፍ ደረጃም ቢሆን እንኳን ሁሉም ፓርቲዎች የወደፊቷ ኢትዮጵያ በህዝቦች መልካም ፍቃድ ላይ የተመሰረተ ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት ዴሞክራቲክ ሀገር ለማድረግ በፓርቲዎቻቸው ሰነዶች ላይ ያሰፈሩ ናቸው:: ስለዚህም አቶ አንዱ አለም ልዩነት ‹ሀ› እና ‹ለ› ብለው ያቀረቧቸው ልዩነቶች መሰረታዊ ችግሮች አይደሉም በመርህ ላይ የተመሰረተ ትብብርን ለመፍጠር::

እርግጥ ነው ዴሞክራሲያዊ ስርአት በሰፈነባቸው ሃገሮች አይደለም በፖለቲካ ፓርቲዎች መሃከል ይቅርና ውስጣዊ ዴሞክራሲ ባለው ፓርቲ ውስጥ እንኳን የሃሳብ ልዩነቶች ይኖራሉ:: እንዲህ ያሉ በሃሳብ ላይ የተመሰረቱ ልዩነቶች ዴሞክራሲያዊ ስርአቱን የሚያበለጽጉና የሰፊውን ህዝብ ተጠቃሚነት የሚያጎለብቱ **ጤናማ ልዩነቶች** ናቸው:: እነዚህ ልዩነቶች በተወሰነ መልኩ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የግብና ስትራተጂ ልዩነቶችን ሊፈጥሩ ይችላሉ:: እነዚህን የግብና ስትራተጂ ልዩነቶች ለማጥበብና በመርህ ላይ የተመሰረት ትብብር ለማድረግ ግን የሚቻልበት መንገድ እጅግ በጣም ሰፊ ነው::

ከዚህ በተቃራኒ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ያለው መሰረታዊውና ትልቁ ልዩነት ከላይ የተጠቀሰውን አይነት ልዩነት አይደለም:: ከላይ የተጠቀሰውን አይነት ጤናማ ልዩነት ቢኖራቸውማ ልዩነታቸውን አክብረው፣ በጋራ የሚያስማማቸው አጀንዳዎችን ነድፈው ሁሉም አካላት በሚያስማማ መልኩ በትግባር በተንቀሳቀሱ ነበር:: እስከዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ፓለቲካ ፓርቲዎች መሃከል ስንት ቅንጅቶች፣ ግንባሮችና ህብረቶች ተቋቋሙ? ስንቱስ የተቋቋሙበትን አላማ አሳኩ? ስንቶቹስ ተጨባጭ ተግባራትን ሳያከናውኑ ከሰሙ? ሁሉም በሚያስብል ደረጃ የተቋቋሙበትን አላማ አላሳኩም:: ምክንቱም ውስጣዊና ተቋማዊ ድክመቶቻቸውን ሳያርሙ፣ በሃሳቦች ዙሪያ ከሚደረገው መቀራረብ ይልቅ በግለሰቦች ዙሪያ ለመሰባሰብ መሞከራቸውና ካለፈው ስህተት እንኳን ለመማርና ለማስተካከል ሳይችሉ በመቅረታቸው ነው:: የየራሳቸውን ግብና የተግባር ቅደም ተከትል በአግባቡ አንጥሮ አለማውጣት፣ ከሌሎች ፓርቲዎች አንጻር ያላቸውን ልዩነት በአግባቡ አለመለየት እና ልዩነት ላይ ሳይሆን በሚያስማሙ አጀንዳዎች ላይ እየሰሩ በሂደት ልዮነቶችን የማጥበብ አካሄድ አለመከተል በመሰረታዊነት የድክመት እንጂ የልዩነት ማሳያዎች ሊሆኑ አይችሉም:: ስለዚህም ***ውስጣዊ ድክመት እንጂ ልዩነት አይደለም መዕከላዊ ቦታ መያዝ*** የሚገባው::

## 2) በበለጠ መብራራት የሚገባቸው ሃሳቦች

### ሀ) አንድ ህዝብ ሲባል፣

አቶ አንዱ አለም ተቃዋሚ ኃይሎች ይለያዩባቸዋል ብለው ካቀረቡት አምስት ሃሳቦች መካከል "የኢትዮጵያ ሕዝብን አንድነት በተመለከተ፤ አንድ ሕዝብ ነን ወይንስ አይደለንም?" የሚለው ቀዳሚው ነው:: "አንድ ህዝብ" ሲባል አንድ አይነት ባህል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ማንነት፣ እና ከአንድ ዘር ወይም ነገድ የመጣን የሚለውን አስተሳሰብ ያዘለ ነው? ወይስ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች የየራሳቸው ቋንቋ፣ ባህልና ማንነት ያላቸው በመከባበርና በመቻቻል ላይ የተመሰረተ አንድነት ያላቸው ህዝቦችን ነው? ለምሳሌ፣ በአሜሪካ የጥቁር ህዝብ አለ፤ እንዲሁም የነጭ፣ የስፓኒሽና ሌሎች ህዞቦች አሉ:: የአሜሪካ ህዝብ የሚለው ስያሜ  ከላይ የተመለከቱትን ህዝቦች በወል በአንድነት የሚገልጽ ነው:: ይህ በብዙ የአለም ሃገራት የሚታይ ተጨባጭ እውነት ነው:: ስለዚህ በመሰረታዊነት በተቃውሞ ኃይሎችና ልሂቃን መታየት ያለበት ጉዳይ እኛ አንድ ህዝብ ነን ወይ የሚለው አስተሳሰብ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ***በምን ላይ የተመሰረተ*** መሆን አለበት የሚለውን ነው::

ምክንያቱም አንደኛ፣ የኢትዮጵያ ዘመናዊ የሃገር ግንባታ ታሪክ እንደማንኛውም የሃገር ግንባታ ታሪክ ያለፈባቸው መሰረታዊ ሂደቶች አንድም ***የተወሰነን ቡድን ወይም ብሔር ልሂቃንን ማዕከል*** (ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ የአማራንና ትግራይን፤ በታይላንድ የታይን፣ በኢንዶኔዥያ የጃቫን ወዘተ) ያደረገ በመሆኑ፣ ***ከሃይማኖት አድሎዊነት ጋር የተያያዘ*** በመሆኑ (በላቲን *Cuius Mgio Eius Religio* ማለትም የህዝቡ ሃይማኖት በመሪው ሃይማኖት የሚወሰን ነው) እንዲሁም የመንግስት ተቋማት ምስረታና መስፋፊት ***የተወሰነውን ማህበረሰብ በሚገፋ ሁኔታ*** የተካሄደ ነበር:: ሁለተኛ፣ የኢትዩጵያ ፖለቲካ አሁንም ደረስ ትልቁ መነሻው ***የሃገር ግንባታ ታሪክና ቁርሾዎች*** ናቸው:: ለምሳሌ ያህል አጼ ሚኒሊክ ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ሃገር ግንባታ ያደረጉትን አስተዋጽኦ በበጎም በክፉም የሚያደርጉትና ባላቸው የታሪክ ምልከታ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ አቋም የሚያራምዱ ብዙዎች ናቸው:: ታሪክ ለታሪክ ምሁራኖች የተተወ ጉዳይ ሳይሆን መሰረታዊ የፖለቲካ አቋም የሚወስን ጉዳይ ነው::

ሶስተኛ፣ እንደማንኛው የሃገር ግንባታ ሂደት ኢትዮጵያም ያለፈችበት ሂደት ***ሁሉንም አካል በሚጠቅም መልኩ አይደለም***፤ ዋናው ቁም ነገር ይህን ሃቅ ተቀብሎ ታሪካዊ ስህተቶችን አርሞ፣ የተዛነፉ የህዝቦች ግንኙነቶችን አስተካክሎ፣ ያለፈውን ታሪክ ለታሪክ ሙሁራን ትቶ የተሻለ ነገን የመፍጠር ሂደት ላይ ማተኮሩ እግጅ አስፈላጊ ነው:: የህዝቦች አንድነት መገለጽ

ያለበት ትላንት በተደረጉ ድርጊቶች ብቻ ሳይሆን በነገ የጋራ ተስፋዎች ጭምር መሆን ይገባዋልና ነው::

**ለ) የሃገር አንድነት እና ሉዓላዊነት**

ሌላው አቶ አንዱ አለም አንስተው በስፋት ያልሄዱበት ጉዳይ "ኢትዮጵያ፤ የቆዳ ስፋቷና ክልሏ ተጠብቆላት፤ አንድ ሀገር ናት ወይንስ አይደለችም?" ነው:: ይህ ሃሳብ የግዛት አንድነት ወይም ፈረንጆች territorial integrity የሚሉት ነው:: በንድፈ ሃሳብ የሃገር አንድነት የሚለው ፅሳቤ ሶስት አስተሳሰቦችን ያካተተ ነው:: አንደኛ፣ አቶ አንዱ አለም ያነሱት **የግዛት አንደነትን** የሚመለከት ሲሆን ይህም በካፒታሊስት ስርአት ማቆጥቆጥና ቀኝ ግዛት መስፋፋት ጋር ተያይዞ የሃገሮችን ድንበር ከየት እስከየት እንደሆነ የማካለል ሃሳብን ሲያመላክት፣ ከሃያኛው ክፍለዘመን አጋማሽ ወዲህ ደግሞ ይህ ሃሳብ የአየርና የባህር ክልልንም የሚያመላክት ሁኖአል:: ሁለተኛው አስተሳሰብ የሚያጠነጥነው **የመንፈስ አንድነት**(spritual unity) በሚለው ዙሪያ ሲሆን ይህም ከአንድነት አስተሳሰብ ውስጥ ህዝቡ ውስጥ ሰርጾ የገባና የቆየና በቅኝ ግዛት መስፋፋት ሂደትም ውስጥ ቀኝ ገዢዎች ሊያጠፉት ሞክረው እንብዛም ያልተሳካላቸው አስተሳሰብ ነው:: ሶስተኛው አስተሳሰብ **የህዝቦች አንድነት** የሚባለው ሲሆን፤ ይህም አስተሳሰብ የሃገሮችን አንድነት በህዝቦች የባህል፣ የቋንቋና ማንነት ተመሳስሎ ላይ የሚያጠነጥን ነው::

የኢትዮጵያ እንደ ሃገር የመቆምና አንድ ሃገር ሆኖ የመቀጠል ጉዳይ መያያዝ ያለበት ከግዛት አንድነት ጋር ብቻ ሳይሆን የመንፈስና የህዝቦች አንድነት ጋር ጭምር መሆን ይገባዋል:: የኢትዮጵያ ሉአላዊነት መገለጽ ያለበት በግዛት አንድነት ሳይሆን በህዝቦቿ አንድነትና የጋራ የወደፊት ተስፋዎች መሆን ይገባዋል:: ለዚህም በስልጣን ላይ ያለውን ኃይል ብቻ ከስልጣን ለማውረድ የሚደረግ ትግል ብቻ ሳይሆን መካሄድ ያለበት ትግል መሰረታዊና ስርነቀል የስርአት ለውጥ ለማምጣት መሆን አለበት:: ስለዚህም፣ የኢትዮጵያ የግዛት አንድነት የሚወሰነውም የተቃውሞ ኃይሎች በጋራ ሊያመጡት በሚችሉት መሰረታዊና ስርነቀል ለውጥ መሳካት ወይም አለመሳካት ነው:: ይህ ምን ማለት ነው?

መሰረታዊና ስርነቀል ለውጥ ሊላበስ ይገባዋል ብዬ ያመንኩባቸውን ሃሳቦች በቀደመው ጹሁፌ አቅርቤያለው:: አሁን ላይ የማተኩረው አቶ አንዱ አለም በነሱት ሃሳብ ላይ ልዩነት ያለኝንና ከላይ የተመለከተውን ጥያቄ ለመመለስ ነው::

I. የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትን ከሚፈታተኑ ነገሮች አንዱና ዋነኛው የመገንጠል እንቅስቃሴ የሚያካሂዱ ሃይሎች መኖራቸው ነው:: የነዚህ ሃይሎች መሰረታዊ መከራከሪያና እምነት **"ለሁሉም ህዝቦች እኩል የሆነችና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ**

**መገንባት አይቻልም**" የሚለው ነው:: ይህም ከኢትዮጵያ ታሪክ እንደሚታየው ስልጣን ላይ ያለው አንድ አናሳ ቡድን ከስልጣን ሲወርድ ሌላው አናሳ ቡድን እንጂ መሰረታዊ የሆነ የማህበራዊ ክፍሎች (social classes) አሊያም አጠቃላይ ማህበራዊ አደረጃጀት (social structure) ለውጥ አልመጣም:: ስለዚህም የሚደረገው ትግል ሌላ አናሳ ቡድን ስልጣን ላይ ለማውጣትና ገዢ ለመቀየር ሳይሆን የህዝቦችን የተለያዩ ፍላጎቶችን አቻችሎ የሚመራና ህዝቡን የሚወክል የአገዛዝ ስርአት ለመዘርጋት መሆን ይገባዋል:: ይህ ከሆነ ለመገንጠል የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ያላቸውን መከራከሪያ የሚያስቀርና ወደ አንድነት ሂደት የሚጎትታቸው ይሆናል::

II. የግዛት አንድነት ብቻውን እንደ ኢትዮጵያ ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ያሉባት ሀገር ይልቅና በሶማሊያም የሃገርን አንድነት ማስጠበቅ አልቻለም:: ይህ አካሄድ በሁሉም የኢትዮጵያ መሪዎች በአንድ መልኩም ይሁን በሌላው ሲደረግ የነበረ ነው:: ይህ አካሄድ ያደረገልን ነገር ቢኖር እዚህ ደረጃ ላይ እንድንደረስ ብቻ ነው:: የኢትዮጵያን የሃገር አንድነት ለማስጠበቅ መሰረታዊ ለውጥ መኖር አለበት ስል የመንፈስና የህዝቦች አንድነትን ጭምር ማምጣት አለብን ለማለት ነው:: የመንፈስና የህዝቦችን አንድነት ካመጣን ከምንፈልገው በላይ የግዛት አንድነታችንን ማስጠበቅ እንችላለን፤ በተጨማሪም ከኤርትራ ጋር የተደረገውን ፍቺ እንደገና ለማደሰም ትልቅ ዕድል የሚከፍት ይሆናል::

III. የመንፈስ፣ የህዝቦችንና የግዛት አንድነት እንዴት ማምጣት ይቻላል? እነዚህ ሶስት የአንድነት አስተሳሰቦች አዋህደን በአንድ ላይ ለማምጣት መስራት ያለብን ነገር የሃገራችንን የፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ ስርአቶች ጥገናዊ ሳይሆን መሰረታዊ ለውጥ መቀየር መቻል አለብን:: እውነተኛ፣ በተቋማት ግንባታ ላይ የተመሰረት፣ ህዝባዊ መሰረት ያለው፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ያሰፈነ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ማስፈንን ይጠይቃል:: ሰፊውን ህዝብ ተጠቃሚ የሚያደርጉና ያሉብንን ችግሮች የሚቀርፉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦችን መፈጸምና ማሳካት ይጠበቅብናል:: ምክንያቱም ድህነት በራሱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊ ችግሮችን የሚያፈልቅና የህዝቦችን ተስፋ የሚገድል በመሆኑ ጭምር ነው::

IV. ከላይ የተጠቀሱትን አላማዎች ለማሳካት ከምንም በላይ ሰላማዊ የትግል ስልት መከተል አስፈላጊና ተገቢ ነው:: ለዚህም ሁለት ሃሳቦችን ማንሳት እፈልጋለው:: አንደኛ፣ በ1997 ምርጫ ተከትሎ ከነሁሉም ችግሮች ተቃዋሚዎች አዲስ አበባን

ቢቀበሉና የአውሮፓ ማህበርና ሌሎች ተቋማት ሊሰጧቸው የነበረውን እርዳት በአግባቡ ተጠቅመም ለውጥ ቢያሳዩ ኑሮ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከነበረበት ደረጃ በትንሹ አንድ ደረጃ ከፍ ይል ነበር:: ሁሉም የየራሳቸውን የፖለቲካ ስልት ሲነድፉ አንድም ብልጭ ብሎ የነበረው ህዝባዊ መነቃቃትና ተስፋ ሲኮሰምን በሌላ በኩል ወደ አንድ መሰባሰብ የነበረው የፖለቲካ ፓርቲዎች ሂደት መልሶ ተበተነ:: አሁንም ድረስ የተቃዋሚ ፖለቲካ ኃይሎች ገዢውን ግንባር ከማብጠልጠል (ለምሳሌ፣ ዶ/ር መራራ አሜሪካ መጥቶ እንደ ትልቅ ስኬት ያነሳው ገዢዎቻችንን መሳደብ ብሎ ነው) በዘለለ የራሳቸውን አማራጭ ለህዝቡ ለማስተዋወቅ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ እምብዛም ነው:: አሚጦ የሰላማዊ ትግል አማራጮችን መጠቀም መቻል አለብን:: ሌላው ቁም ነገር እስካሁን እኔ እስካለኝ መረጃ ድረስ በትጥቅ ትግል ስልጣን የተቆናጠጡና ዴሞክራሲዊ ስርአትን ያሰፈኑ ኃይሎችን አላቅም:: እንደማስበው ከሆነ ግን ይህ የሆነበት ምክንይት ጦርነት በራሱ ግቡ ***ሁሉንም አሸናፊ የማያረግና*** ከጦርነት በኃላ ***እነርሱ(ጠላት) እና እኛ*** የሚል አስተሳሰብ የሚያሰፍን በመሆኑ ነው:: ይህም ጸረ-ዴሞክራሲያዊ ባህል እንዲያብብ እድል የሚከፍት ነው::

V. ሁለተኛ፣ አቶ አንዱ አለም ሁለት የተለያዩ ነገሮችን አንስተዋል:: በእርግጥ የጸረ-ቀኝ ግዛት እንቅስቃሴዎች በአብዛኛው የትጥቅ ትግል ላይ የተመሰረቱ ነበር:: ነገር ግን፣ የጸረ-ቀኝ ግዛት እንቅስቃሴዎች አላማቸው ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለማስፈን አልነበረም:: እንደውም በአብዛኛው ከነጻነት በኃላ ስልጣን ላይ የወጡት ሰዎች በገዢዎቻቸው ሃገር ትምህርት የተማሩና በቀኝ ግዛት አስተዳደር ውስጥ ለመሳተፍ አላማ የነበራቸው፤ ነገር ግን ከፍተኛው የቀኝ ግዛት አስተዳደር ስልጣኖች ለቀኝ ገዢዎቻቸው የተተወ በመሆኑ የስልጣን መሰላሉ ላይ ወደ ላይኛው እርከን ማደግ ባለመቻላቸው ቅር የተሰኙ ሰዎች ናቸው:: በሌላ በኩል፣ ጋናን እና ደቡብ አፍሪካን እንዲሁም ዛሬ የተሻለ ዴሞክራሲ አለባቸው የሚባሉ ሃገሮችን የሚመለከት ሰው የሚገነዘበው ነገር ቢኖር ከአንባገነንና ከአፓርታይድ ስርአት ወደ ተሻለ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ያመሩበት መንገድ ስላማዊ ትግል ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ነው:: ስለዚህም የዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለማስፈን የሚደረግ ትግል ከጸረ-ቀኝ ግዛት ትግል ጋር ማመሳሰሉ በጣም አስቸጋሪ ነው::

VI. በሰላማዊ ትግል ውጤታማ ለመሆን መደራጀት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው:: ነገር ግን የኛ መደራጀት ወይም መሰባሰብ በምን መልኩ መሆን አለበት? የሚለው ጥያቄ መሰረታዊ ነው:: ዶ/ር ፍሰሃ እሸቱ በቅርቡ ባወጣው ጹሁፉ ላይ ጋዜጠኛ እስክንድር

ነጋን እንደአሰባሳቢና መሪ እንዲሆን ያቀረበው ፕሮፖዛል አለ:: ጋዜጠኛ እስክንድር በመሰረቱ ከማደንቃቸው ወጣትና በሳል ጋዜጠኞች መካከል አንዱ ነው:: ሆኖም፣ ጥያቄው ***በግለሰቦች ዙሪያ ወይስ በሃሳብ፣ በትግል ግብና ስትራተጂ ዙሪያ*** ነው መሰባሰብ ያለብን? የሚለው ነው:: እንደኔ እስካሁን ድረስ ከገመገምኳቸው 13 የፖለቲካ ፓርቲዎች ፕሮግራም አንጻር ስመለከተው መሰባሰብ ያለብን በሃሳብ ዙሪያ ነው ባይ ነኝ:: ከጥቃቅንና ከቃላት አጠቃቀም የዘለለ መሰረታዊ ልዩነቶችን አላገኘሁም:: ባጠናኲቸው ፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ያገኘሁት መሰረታዊ ልዩነቶች የግለሰቦች ቅራኔና ***ማን መሪ ሊሆን*** የሚል የስልጣን ስኩቻዎች ናቸው:: ይህም የደካማ ተቋማዊ አደረጃጀት ነጸብራቅ ነው:: ስለዚህ፣ በተቃውሞ ፖለቲካ ልሂቃኖች መካከል ያለውን ግለሰባዊ ቁርሾ ወደ ጎን አድርገን፣ ትልቁን ሃገራዊውን ምስል ተመልክተን፣ አንድ በሚያደርጉን ሃሳቦች ዙሪያ ተደራጅተን በሂደት ልዩነታችንን በማጥበብ፣ የተቃውሞ ሂደቱን ተቋማዊ አድርገን፣ ጠንካራ፣ግልጽና ተጠያቂነት የሰፈነበትን አደረጃጀትና አሰራር ዘርግተን ተቃውሞውን መምራት መቻል አለብን::

*(ይህ ጹሁፍ አቶ አንዱ አለም ተፈራ "የተቃዋሚ ፖለቲካ ኃይሎች የተግባር ድክመት ወይንስ የግብና የእቅድ ልዩነት" በሚል በጻፉት ጹሁፍ ላይ ተመስርቶ የተጻፈ ነው::)*